የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች (ፍኖተ ካርታ): ግምገማ

# ክፍል አንድ፡- ራእይና ፍልስፍና

የግል አስተያየት

በነጋ ወርቁ ደበላ (ፕሮፌሰር)

©2019

## ማውጫ

**ክፍል አንድ፡- ራእይና ፍልስፍና** .......... 1

መግቢያ .......... 3

የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች (ፍኖተ ካርታ) .......... 4

ራእይ: .......... 5

የትምህርት ፍልስፍና .......... 5

**የፍኖተ ካርታ የትምህርት ፍልስፍና** .......... 6

የኔ አስተያየት (በትምህርት ፍልስፍናው ላይ) .......... 6

ብቁ ዜጋ ማዘጋጀትን በተመለከተ፤ .......... 6

*በፌደራል መንግስት ደረጃ፤* .......... 6

*በእስቴት መንግስት ደረጃ፤* .......... 6

*በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤* .......... 7

*በህብረተ ሰብ ደረጃ፤* .......... 7

*በብዙሃን መገናኛዎች ደረጃ፤* .......... 7

*በቤተሰብ ደረጃ፤* .......... 7

*በትምህርት ቤት ደረጃ፤* .......... 7

*በተማሪ ደረጃ፤* .......... 7

**ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች ማፍራት በተመለከተ፤** .......... 7

*በፌደራል መንግስት ደረጃ፤* .......... 7

*በእስቴት መንግስት ደረጃ፤* .......... 7

*በትልልቅ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ፤* .......... 8

ብዝሃነትን ላካተተው አገራዊ አንድነትን በተመለከተ .......... 8

References: .......... 8

EDUCATIONAL CENTER

# መግቢያ

የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን እና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን (ፍኖተ ካርታ)አስመልክቶ የማቀርበው ጽሁፍ ክፍል አንድ በራእይና በትምህርት ፍልስፍና ላይ ያተኩራል። የሚቀጥሉት ተከታታይ ምእራፎች በእያንዳንዱ አብይ ችግርና መፍትሄዎቻቸው ላይ ያተኩራሉ።

**<u>ስለኔ ባጭሩ፤</u>** እኔ አንደኛ ደረጃ ባልቻ አባነፍሶ ትምህርት ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃ ልኡል መኮንን ትምህርት ቤት (በሶስት አመት) አጠናቅቄ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመግባት የባችለር ኦፍ ኢዱኬሽን ትምህርቴን በማእረግ አጠናቅቄአለሁ። ከአስመራ ዩኒቨርሲቲም በአካውንቲንግ የባችለር ዲግሪ ተመርቄአለሁ። ከዛም በብሪቲሽ ካውንስል አማካኝነት በኢትዮጵያ ለነበሩት የመምህራን ማሰልጠኛ የእንግሊዝኛ አስተማሪዎች ለመጣው የትምህርት እድል በመወዳደርና በአሸናፊነት በመወጣት ሊድስ(እንግሊዝ) በሚገኘው የሊድስ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪዬን እንድሰራ እድል ገጥሞኝ በመማር ዲግሪውን ተቀብያለሁ። በመቀጠልም በአለም አቀፉ የአውስትራሊያ የትምህርት እድል (Overseas Postgraduate Research Scholarship) በግል በመወዳደርና አሸናፊ በመሆን የዶክተር ኦፍ ፊሎሶፊ ዲግሪዬን ከአደለይድ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ሶሲዮሎጂ ተቀብያለሁ። ከዚሁ ከአሜሪካም በኢንፎርሜሽን ሲስተም በማስተርስ ዲግሪ ከማርሻል ዩኒቨርሲቲ ተመርቄአለሁ።

የስራ ልምድን በተመለከተ፣ በአስመራ የመምህራን ማሰልጠኛ 7 አመት፣ በአስመራ ዩኒቨርሲቲ 1 አመት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 2 አመት፣ በባችለር ኮሌጅ (አውስትራሊያ) 1 አመት፣ በተለያዩ የአውስትራሊያ ዩኒቨርሲቲዎች በቱተርነት ለ 3 አመት፣ በማርሻል ዩኒቨርሲቲ (አሜሪካ) 18 አመታት አገልግያለሁ። አሁንም በማስተማር ላይ እገኛለሁ። በአሁኑ ሰአት በዶክቶራል ፋክልቲነት በሙሉ ፕሮፌሰርነት ማእረግ እያገለገልኩ፣ በትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ትኩረቱን በ ESL ላይ ያደረገውንም ፕሮግራም መሪ ነኝ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በአውስትራሊያ ካቶሊክ ዩኒቨርሲቲም የዶክትሬት ፕሮግራም የውጭ ፈታኝ (external examiner) በመሆን አገልግያለሁ። በዚህ በአሜሪካም የዶክተር ነጋ የትምህርት ማእከል (https://drnegaeducationcenter.org/) የተሰኘም ድርጅት በ2013 አመት ምህረት

አቋዋቁሜአለሁ። ለአማርኛ ማስተማሪያ የሚሆንም ድህረ ገጽ (https://www.ethioeducation.com/) አዘጋጅቻለሁ።

በቅድሚያ ይህንን ፍኖተ ካርታ ለመስራት ሙህራዊ ክሎታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን አጥፍተው ላዘጋጁት ሰዎች ታላቅ ክብርና ምስጋናን ላቀርብ እወዳለሁ።

ያለኝን አስተያየት እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች (ፍኖተ ካርታ)

| | |
|---|---|
| የተዘጋጀበት ቀን: | ሰኔ 2010 ዓም. |
| የተዘጋጀበት ቦታ: | በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ጊዜያዊ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ትምህርት ሚኒስቴር |
| የገጽ ብዛት፡ | 82 |
| የተሳታፊ ብዛት፡ | >100 |

በቅድሚያ ይህንን ፍኖተ ካርታ ለመስራት ሙህራዊ ክሎታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን አጥፍተው/ ኢንቬስት ላደረጉ፣ ላዘጋጁ፣ ሰዎች ታላቅ ክብርና ምስጋናን ላቀርብ እወዳለሁ።
ይህን ጽሁፍ የሚያነብ እንዲያውቅልኝ የምፈልገው የዚህ ጽሁፍ አላማ የ 'ሮድ ማፕ' ጸሃፊዎችን ለማናናቅ፣ ለማሳነስ፣ ለማስጠየፍና፣ ዋጋ ለማሳጣት፤ ባንጻሩ ደግሞ ራስን ለመካብ፣ የ15 ደቂቃ ዝና ለማትረፍ ሳይሆን ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ ችግራችንን በጋራ ለመፍታት የተሰነዘረ ወንድማዊ የግል አስተያየት መሆኑን ነው። ሃሳብ ተገቢ፣ ተሻጭ፣ ተቀያሪ፣ ተቀናሽ፣ ተደማሪ፣ በከፊል ተቀባይ ወይም ተለዋጭ የሆነ የማይጨበጥ ቁስ

| |
|---|
| አካል መሆኑን ተገንዝበን እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ የሚል ግትርነት በኔ በኩል እንደሌለ ከወዲሁ ስግለጥ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ግለሰብም ይህን በቅጡ እንዲረዳልኝ አሳስባለሁ። አሁን ያለንበት ጊዜ እርስ በርስ የሰላ ትችት የምናቀርብበት ሳይሆን ተፎካካሪ ሃሳቦችን በጋራ ገምግመን የተሻለውን በጋራ የምንመርጥበት ነው። ይህ ፍኖተ ካርታ ገና ያልተጠናቀቀና ገንቢ ሃሳቦችን በማሰባሰብ ላይ ስለሆነ ይህ አስተያየት እንደ አንድ ዜጋ በግል ሃሳቤን ለመስጠት ያደረኩበት ሙከራ ነው። |

# ራእይ:

| | |
|---|---|
| የፍኖተ ካርታ ራእይ: | አሁን እያዘጋጀነው ያለው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የአገራችን የመካከለኛ ገቢ ራእይ ለማሳካት የሚያስፈልገውን ብቁ የሰው ኃይል በብቃትና በብዛት እንዴት በማፍራት የአገራችንን ሁለንተናዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ግንባታ ሥራዎች መደገፍ እንዲቻል ከአለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማስተሳሰር የሚዘጋጅ ዝርዝር እቅድ ነው፡፡ |
| የፍኖተ ካርታውን ራእይ በተመለከተ የኔ አስተያየት | የፍኖተ ካርታውን ራእይ በተመለከተ እኔም የአዘጋጂዎቹን ራእይ እጋራለሁ። |

# የትምህርት ፍልስፍና

የትምህርት ፍልስፍና ትልቁን የአገሪቱን የትምህርት ስእል የሚያሳይ ነው።

| | |
|---|---|
| ችግሩ | የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በበርካታ ችግሮችና ተግዳሮቶች የተሞላ ነው፡፡ |

EDUCATIONAL CENTER

## የፍኖተ ካርታ የትምህርት ፍልስፍና

- ዜጐች በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብቁና በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ አድርጐ አጠቃላይ ሰብእናቸውን መገንባት፣
- ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ እና ለሕግ ዘብ የቆሙ ዜጐችን ማፍራት፣
- ብዝሃነትን ላካተተው አገራዊ አንድነትና ሠላም ዘብ እንዲቆሙ ማድረግ፣

## የኔ አስተያየት (በትምህርት ፍልስፍናው ላይ)

የተለያየ አይነት የትምህርት ፍልስፍና  መኖሩ ግልጽ ነው[1]። የፍኖተ ካርታው የትምህርት ፍልስፍና ይህንን አይነት ፍልስፍና እከተላለሁ የሚል ስም ያለው ፍልስፍና በግልጽ ባይጻፍም ህልሙንና የፍልስፍናውን ዝርዝር በማየት በ'ሶሻል ሪኮንስትራክሽንኢዝም' (ህብረተስብን መልሶ መገንባት) ፍልስፍና ላይ መሰረት ያለው ይመስላል። ምክንያቱም በ'ሪኮንስትራክሽንኢዝም' እይታ፣ ትምህርት የማህበራዊ (ሶሻል) ችግሮችን የሚፈታ መንገድ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። በከፊል ደግሞ ማህበራዊ ባህርይ (ቢሄቨየርኢዝም) ላይም (ለምሳሌ መልካም ዜጋን ማፍራት)መርኮዝ ያለ ይመስላል። በአብዛኛው ህዝባችንም ሆነ በሌላው አለም (ለምሳሌ የአሜሪካ የህዝብ [መንግስት]ትምህርት ቤቶች) ኢሴንሻሊዝም (መሰረታዊና ለህይወት ጠቃሚ ትምህርት)ላይም መመርኮዙ ጠቃሚ ይመስለኛል - በአገሪቱ አሁን የምናየውም ይሄው ይመስለኛል። እንደዛሬ 40 አመት ፍልስፍና (ማርክሲዝም ባንድ ጎራ ካፒታሊዝም በሌላ ጎራ ተብሎ) ባያጣላንም መመካከሩ ሸጋ ነው። ጠቀሜታ እስካለው ድረስ የተለያዩ አመለካከቶችን ማስተናገዱ ብልህነት ነው።

ከላይ የተገለጸውን ራእይ እውን ለማድረግ በቾክና በቃል በሚሰጥ ትምህርት ብቻ፣ ወይም በወረቀት ላይ ብቻ በተጻፈ መመሪያ፤ ወይም በትምህርት ሚኒስቴር ብቻ በሚደረግ ጥረት ይሳካል ብዬ አላምንም። ሁሉን የህብረተሰብ ክፍል (ባለድርሻ) ያቀፈ መፍትሄ ያሻዋልና።

## ብቁ ዜጋ ማዘጋጀትን በተመለከተ፤

የፍኖተ ካርታ አዘጋጂዎቹ የትምህርት ፍልስፍና መፍትሄ ሃሳብ እንዳለ ሆኖ፤ጥሩ ዜጋ የምናፈራው በክፍል ውስጥ በሚሰጥ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በፌደራል፣ በእስቴት (ይህ ቃል የተመረጠው 'ክልል' ከሚለው  ቃል ይልቅ ገለልተኛ ቃል ስለሆነ ነው) ፣ በህብረተ ሰብ ደረጃ፤ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣  በተማሪ ደረጃ እንዲሁም በሌሎች ባልተጨመሩ ጥምር ትብብር የተደረገበት ጊዜ ብቻ ነው።

የባለ ድርሻዎች ሚና፤

*በፌደራል መንግስት ደረጃ፤* በፌደራል ደረጃ መንግስት በራሳቸው የሚተማመኑ በምክንያትያዊ ትንተና የሚያምኑ በአለም አቀፍ ደረጃ አገር የሚወክሉ ሃላፊዎችን በየስራው መመደብ ትምህርት ሚኒስቴርን ጨምሮ። ይህንንም በአገራዊ የመገናኛ ዘዴዎች አስረግጦ መናገርና ህብረተሰቡ እንዲረዳው ማድረግ። የግልና የመንግስት የመገናኛ ዘዴዎች ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ።

*በእስቴት መንግስት ደረጃ፤* በእስቴት ደረጃም ብቃትና ችሎታ ያላቸው አካባቢውንና የአገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ በምክንያትያዊ ትንተና የሚያሳምኑ በራስ መተማመን ያላቸውን ግለሰቦች በሃላፊነት ማስቀመጥ። የእስቴቱ የመገናኛ ዘዴዎች ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ። የእስቴቱን ነዋሪዎች እንዲረዱት ማድረግ። ብቃትና ችሎታ ያላቸውን መምህራን አሰባስቦ በእስቴት ደረጃ በኮንፈረንስ መልክ ስለ ብቁ ዜጋ ማወያየት።

*በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤* ከየእስቴቱ በባህሪያቸው ለምሳሌነት የሚጠቆሙትን መምህራን፤ ተማሪዎችና የትምህርት ድጋፍ ሰጭዎች በአገር ደረጃ እውቅናና ሽልማት መስጠት።

*በእስቴት የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤* በእስቴት ደረጃ ካለባቸው የስራ ግዴታ ውጭ ልዩ የዜግነት ሚናን ለተጫወቱ መምህራን፣ ተማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እውቅናንና ሽልማት መስጠት።

*በህብረተ ሰብ ደረጃ፤* ህዝብ በብዛት በተሰበሰበባቸው አካባቢዎች ለህብረተሰቡ በራሳቸው ፍቃድ ጊዜአቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በነጻ ለሰጡ ሰዎች እውቅናና የአክብሮት መግለጫ ጭብጨባና ሙገሳ ማሳየት ሽልማት መስጠት።

*በብዙሃን መገናኛዎች ደረጃ፤* የራሳቸውን እውቀት፣ ጊዜና ጉልበት ለአገር፣ ለወገን፣ ለሰፈር፣ ለሆስፒታል ታማሚዎች፣ ለደካሞች፣ ለአዛውንቶች፤ ለህጻናት በግልና በድርጅት መልክ አስተዋጽኦ ላደረጉ እውቅናና ሙገሳ፣ ሽልማት መስጠት።

*በቤተሰብ ደረጃ፤* እናትና አባት፣ ታላቅ ወንድምና እህት፣ በልጅ ትምህርት ዋንኛውን ሚና የሚጫወቱ ስለሆነ ተማሪዎችን ጥሩ ዜግነት እንዲያሳዩ መምከር፣ ሲያሳዩ ማመስገንና መሸለም። በገበታ ጊዜም ለውይይት ማቅረብ።

*በትምህርት ቤት ደረጃ፤* በመምህራን የተመረጡ ብቃትና ችሎታ ያላቸው መምህራንን በሳብጀክት/ትምህርት ሃላፊነት መምረጥ። በአርአያነት በጥሩ ዜግነት ተምሳሌነት ያላቸውን መምህራን በየወሩ 'የጥሩ ዜጋ' ተሸላሚዎችን በአስተማሪዎች ማስመረጥ።

*በተማሪ ደረጃ፤* የጠፋ እቃ የመለሱ፣ ለተጎዳ ወገን የረዱ፣ በግል አነሳሽነት ይሁን በሃላፊነት ከትምህርት ውጭ ልዩ አገልግሎት ለሰጡ ተማሪዎች እውቅናና ሽልማት በየሳምንቱ መስጠት።

## *ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች ማፍራት በተመለከተ፤*

ይህንን የትምህርት ፍልስፍና (*ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፤*) እንደ ግብአት ቆጥረን እመሬት ለማውረድ የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች ማካተቱ አማራጭ የለውም።

*በፌደራል መንግስት ደረጃ፤* ለተለያዩ ሥራ ፈጣሪና፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂ ትልልቅ ፕሮጀቶች የሚሆን ፈንድ (ባጀት) መመደብ። ፕሮጄቶቹን አወዳድሮ ፋይናንስ ማድረግ።

*በእስቴት መንግስት ደረጃ፤* የሳይንስና የኢንደስትሪ ማእከል መክፈት። ከባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፤ ፊዚክስና ኤንጂነሪንግ ምሩቃን መርጦ የሳይንስና የኢንደስትሪ ማእከላትን እንዲጎበኙ እድል መስጠትና የስራ ሃላፊነት መስጠት። ጥራትና ብዛቱ ለምሳሌነት ከታች እንደሚታየው የሳይንስና የኢንደስትሪ መክፈት አቅም ካነሰ ከኢንደስትሪ ፓርክ አካባቢ ክፍቶ የሚገኙትን ለጊዜው የሳይንስና የኢንደስትሪ ምንጭች መጠቀም።የሳይንስና የኢንደስትሪ ማእከል ራሱን እንዲችል መጠነኛ የመግቢያ ሂሳብ በማስከፈል ማጠናከር ይቻላል። ከአደጉ የሳይንስና የኢንደስትሪ ማእከላትም ልምድና የቁሳቁስ መቀያየር ማድረግ ይቻላል።

EDUCATIONAL CENTER

https://www.cosi.org/

***በትልልቅ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ፤*** በባዮሎጂ ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስና ኤንጂነሪግ ክፍለ ትምህርት ለሚገኙ መምህራንና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለዚህ የሚሆኑ የመማሪያ መሳሪያዎች እንዲሰሩ ፈንድና (በጀት) የመስሪያ ቦታ መፍቀድ።በዚህ በአሜሪካ በጣም ትልልቅ የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ይህን ዘዴ እንደ ትልቅ እስትራቴጂ ይጠቀሙበታል የወደፊት ገቢያቸውን ለመጨመር።

## ብዙሃንነትን ላካተተው አገራዊ አንድነትን በተመለከተ፤

ኢትዮጵያ የብዙ ቋዋንቋዋ ተናጋሪ ህዝቦች፣ የተለያዩ ድንቅ ህብረ ባህሎች፣ የተለያዩ የእምነት መሰረቶች ያሉባት ህብረብሄር አገር ነች። ብዙሃንነትን ያካተተ አንድነትን መሰረት ያደረገ የትምህርት ስርአት ለመገንባት ባለድርሻዎች ተገቢውን ሚና መጫወት ይገባቸዋል።

***በዩኒቨርሲቲ ደረጃ፤*** *ብዙሃንነትን ያካተተ አንድነት ላይ ያተኮረ የህብረ ባህል ትምህርት (መልታይ ካልቸራል ኢዱኬሽን)በሰለጠነው አገር እንደሚደረገው እንደ አንድ ኮርስ መስጠት።*

***በትምህርት ቤት ደረጃ፤*** *የባህል፣ የቋዋንቋዋ ፣የእምነት፣ የአካባቢ (ኢንቫይሮንመንት) ልዩነቶች መኖሩን ተገንዝቦ በመከባበር፣ በመረዳዳት ፣ በመደማመጥ፣ በችኩልነት ከመፍረድ ልዩነቶችን እያጠበቡ አንድነትን እያጎለበቱ እንዲሄዱ በአመት ሶስት አራት ጊዜ የባህል ዝግጅቶችን፣ ንግግሮች፣ ውይይቶች ማከናወን።*

# References:


[1] Lynch, Matthew (2017). 5 Things That Educators Should Know About the Philosophy of Education, The Edvocate.

https://www.theedadvocate.org/5-things-that-educators-should-know-about-the-philosophy-of-education/